# 5 ብቸኛ የሆኑ ጥገኝነት ጠያቂ ልጆች

## የእድሜ አለመግባባቶች

ዩ.ኬ

ዩ.ኬ ውስጥ ጥገኝነት ለመጠየቅ ሲመጡ እድሜዎት ከ18 አመት በታች ከሆነ **በተቻለው ፍጥነት ይሄን ማለትዎ** እጅግ አስፈላጊ ነው። **አስቀድሞ በወረቅት ላይ የእርስዎን እድሜ እንዲያሳዩ ይጠየቃሉ።**

በዩ.ኬ ህግ መሰረት፣ እድሜው ከ18 አመት በታች የሆነ ታዳጊ እንደልጅ ተቆጥሮ ልዩ የሆነ ድጋፍ ያገኛል። ከ18 አመት በታች ሆነው ያለ ወላጅ ወይም እርሶን ሊንከባከብ ከሚችል አዋቂ ሰው ጋር ሳይሆኑ ወደ ዩ.ኬ ከመጡ "**ብቸኛ የሆኑ ጥገኝነት ጠያቂ ልጅ**" እንደሆኑ ነው የሚታሰቡት።

### የመጀመሪያው እድሜ ግምገማ

የሃገር ውስጥ ጉዳይ ቢሮ ከ18 አመት በታች (እድሜዎ 17 ወይም ከዛ ያነሰ) እንደሆኑ ካላመነ፣ "የመጀመሪያ የእድሜ ግምገማ" ያደርጋሉ፤ **ይሄም የሚሆነው አብዛኛውን ጊዜ 40 ደቂቃዎችን በሚፈጅ አጭር ቃለ-መጠይቅ ነው።**

ከ18 በታች ይሁኑ አይሁኑ የሚወስኑትም **በገፅታዎ** እና **በሚያሳዩት ባህሪ** እንዲሁም **ለሚጠየቁት የተወሰኑ ጥያቄዎች በሚሰጡት መልሶች** ነው። ይሄም የሚሆነው ዩ.ኬ እንደደረሱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው፤ ሊደክሞትም ይችላል። ስለዚህ ለዚህ ነገር መዘጋጀቱ መልካም ነው።

### ምን ጥያቄዎች ይጠይቃሉ?

?

በዚህ አጭር ቃለ መጠየቅ እድሜዎ ስንት እንደሆነ ይጠየቃሉ። በተጨማሪም ስለጉዞዎ፣ እድሜዎትን እንዴት እንዳወቁ እንዲሁም ወደ ዩ.ኬ ለምን እንደመጡ ይጠየቃሉ።

**የልደትዎን ቀን አይገምቱ** – ይሄ በጣም አስፈላጊ ነው። የተወለዱበትን ትክክለኛ ቀን ካላወቁ፣ እድሜዎትን እንዴት እንዳወቁ ያብራሩ። ምናልባትም እነዚህንም ጥያቄዎች ሊጠየቁ ይችላሉ፦

- የተወለዱበትን ቀን እና እድሜዎትን
- ከሐገርዎት ሲወጡ ስንት አመትዎ ነበር? ለምሳሌ፦ እኔ ከሐገሬ የወጣውት ባለፈው አመት 15 አመቴ እያለ ልክ ረመዳን እንዳለፈ ነው፤ ስለዚህ አሁን 16 አመቴ ነው።
- ከትምህርት ቤት ሲወጡ ስንት አመትዎ ነበር?
- ወንድሞችህ/ሽ እና እህቶችህ/ሽ ስንት አመታቸው ነው? ለምሳሌ፦ እኔ በቅርቡ 18 አመት የሞላው የሁለት አመት ታላቅ ወንድም አለኝ፤ ስለዚህ እኔ 16 እንደሆንኩ አውቃለው።
- አካላዊ ወይም አይምሯዊ የጤና እክል ካለብዎት ወይም
- ወደዚህ ሲመጡ ባለፏቸው ሃገራት ልክ እንደ ጣሊያን እና ፈረንሳይ ባሉ ሃገራት ከ18 አመት በታች ሆነው ተቆጥረው እንደሆነ ቢነግሩን።

በተጨማሪም ምንም እንኳን አብረዋቸው ለመኖር ባያቅዱ እንኳን ዩ.ኬ ውስጥ ዘመድ ካለዎት፣ ይሄን ቃለመጠይቅ እና የማጣሪያ ቃለመጠይቅ ለሚያደርጉልዎት ሃላፊዎች ማሳወቁ አስፈላጊ ነው።

### ማስረጃ ሊኖርዎት ያስፈልጋል?

እንደ **ፓስፖርት**፣ **መታወቂያ ካርድ** ወይም **የልደት ካርድ** ያሉ ስለእድሜዎ ማንኛውም ማስረጃ የሚሰጡ ሰነዶች ካለዎት (ዋናውም ወይም ኮፒ) ፣ ለሃላፊዎች በቻሉት ፍጥነት ማሳወቅ አለብዎት። በመጀመሪያው የእድሜ ግምገማ ላይ ሰነድ ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል፤ አንዳንዴም ሰዎች እነዚህን ሰነዶች እንዲያሳዩ አይፈቀድላቸውም፤ ሆኖም ግን በመጀመሪያው "የእድሜ ግምገማ" ላይ ወጣት ሆነው ከተገኙ እነዚህ ሰነዶች የእርሶን ጉዳይ ሊያግዙዎት ይችላሉ።

ልጆችም ጥገኝነት የመጠየቅ መብት ስላላቸው፤ ይሄም ለእርስዎ የጥገኝነት ጥያቄ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

### እድሜዎትን እንደተቀበሉት በምን ሊያውቁ ይችላሉ?

ከመጀመሪያው የእድሜ ግምገማ በኋላ፣ የሃገር ውስጥ ጉዳይ ቢሮ እነዚህን ነገሮች ይወስናል፦

1. ከ18 አመት በታች መሆንዎን እንደተቀበሉ ወይም
2. ወጣት (ከ18 አመት በላይ) እንደሆኑ እንዳሰቡ
3. ተጨማሪ መረጃ እንደሚፈልጉ።

ቢሮው ከ18 አመት በታች እንደሆኑ ካመኑ ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ከሌሎች ልጆች ጋር በአንድነት ወደሚኖሩበት ማረፊያ ይወሰዳሉ። ሌላ ረዘም ያለ የእድሜ ግምገማም ሊወስዱ ይችላሉ። የሚወሰዱበትም ማረፊያ ቦታ በዩ.ኬ የትኛውም ቦታ ውስጥ ሊሆን ይችላል።

**ቢሮው ከ18 አመት በታች መሆንዎን ካልተቀበሉ ደግሞ ሌሎች ወጣቶች ወዳሉበት ማረፊያ ይወሰዳሉ፤ ሌሎች ወጣቶች በሚታዩበትም መንገድ ይታያሉ።**

### የሃገር ውስጥ ጉዳይ ቢሮ እድሜዎት ከ18 በታች መሆኑን ካልተቀበለ ምን ማድረግ ይችላሉ?

**በቻሉት ፍጥነት በወጣቶች ማረፊያ ውስጥ ላሉ የቢሮው ሰራተኞች፣ ዶክተር ወይም ነርስ ወይም ደግሞ እርሶን እየደገፈ ላለ የትኛውም ድርጅት እድሜዎት ከ18 እንደሚያንስ ሊነግሩዋቸው ይገባል።** "ማይግራንት ኸልፕ" ለተባለው በጎ አድራጎት ድርጅትም ሊያሳውቁ ይገባል። ይሄ በጎ አድራጎት ድርጅትም ወደ አካባቢው ባለስልጣን እንዲወስድዎት ወይም ደግሞ **ለእድሜ ግምገማ የማህበራዊ ሰራተኛ ማየት እንደሚፈልጉ** ልታሳውቁ ይገባል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ሊረዳዎት የሚችለውን "ሂዩማንስ ፎር ራይትስ ኔትዎርክ"ንም ሊያናግሩ ይገባል። በ **00447506663089** ላይ ሊያገኝዋቸው ይችላሉ። በዩ.ኬ ውስጥ በስህተት እንደወጣት የታዩ ልጆችን የሚረዳ ልዩ ድርጅት ነው።

**እንዳለመታደል ሆኖ ዩ.ኬ ውስጥ አብዛኛዎቹ ከ18 አመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች እንደትልቅ ሰው እየታዩ ነው። ይሄም እርስዎ ያደረጉት የተለየ ጥፋት ኖሮ ወይም ጉዳዩ ግላዊ ሆኖ አይደለም። ማድረግ የሚቻለው ስለእድሜዎት የተወሰነውን ውሳኔ ለመጋፈጥ መሞከር ነው።**

**ደረጃ 1**

You arrive in the UK and claim asylum. you tell them you are under 18 as soon as possible. you will be asked how old are you soon after you arrive.

**ደረጃ 2**

You will have an initial age assessment which means that someone will decide whether or not they think you are under 18 based on how you look and how you act in the interview.

አንዳንድ ሰዎች ላይ ይሄ ግምገማ አይካሄድም ምክንያቱም ሃገር ውስጥ ጉዳይ ቢሮ እድሜዎን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ብሎ ስለማያስብ ነው። ይሄ ከተፈጠረም ወደ ልጆች ማረፊያ ይወሰዳሉ። የአካባቢው ባለስልጣንም ይከታተልዎታል።

**አማራጭ 2**: የሃገር ውስጥ ጉዳይ ቢሮ ከ 18 አመት በታች እንደሆኑ አላመነም።

ልክ እንደ ሆቴል ወይም ካምፕ ያሉ **የወጣቶች ማረፊያ ይወሰዳሉ ፤ ሌሎች ወጣቶች በሚታዩበትም መንገድ ይታያሉ**። ይህን ውሳኔም ይግባኝ ለማለት ይረዳዎት ዘንድ በቻሉት ፍጥነት ጠበቃ ወይም ሂዩማንስ ፎር ራይትስ ኔትወርክን ማናገር አለብዎት።

ባሉበት ማረፊያ ውስጥ ላሉ ሰራተኞች ወይም ዶክተሮችን ማግኘት ከቻሉም ለእነሱ ማሳወቅ አለብዎት።

**አማራጭ 1:** የሃገር ውስጥ ጉዳይ ቢሮ ከ18 አመት በታች እንደሆኑ አምኗል።

**ደረጃ 3**

ወደ አካባቢው ባለስልጣን ዘንድ ይላካሉ፤ እነሱም ብቸኛ የሆኑ ጥገኝነት ጠያቂ ልጅ እንደሆኑ አድርገው ይቆጥርዎታል። የአካባቢው ባለስልጣንም ልጅ እንደሆኑ እንደማያስቡ እና የእድሜ ምዘና ማድረግ እንደሚፈልጉ መግለፅ ይፈቀድላቸዋል።

**Option 2:** The local Authority doesn't believe that you are under 18 and conduct an age assessment

**Option 1:** The Local Authority believes that you are under 18.

ብቸኛ የሆኑ ጥገኝነት ጠያቂ ልጅ እንደሆኑ ተደርገው ይቆጠራሉ። አስታውሱ: የሃገር ውስጥ ጉዳይ ቢሮ ይሄን ውሳኔ ይግባኝ ማለት ይችላል።

የሃገር ውስጥ ጉዳይ ቢሮ ውሳኔውን ይግባኝ እንዳለ ከተነገርዎት፣ በቻሉት ፍጥነት የሚያግዝዎትን ጠበቃ ማግኘት አለብዎት።

HUMANS FOR RIGHTS NETWORK

**ኤቼ ኤፍ አር ኤንን በ 0044750663089 ቁጥር በዋትስ አፕ፣ በፅሁፍ መልእክት እና በስልክ ማግኘት ይችላሉ።**

CHANNEL INFO PROJECT

Refugee Legal Support

HUMANS FOR RIGHTS NETWORK